Ethio-Cult Information Centre e.v.
Germany

22.09.2006

ለተከበራችሁ ውድ ኢትዮጵያኖች: ሰላም ለእናንተና ለቤተሰባችሁ እንዲሆን ከልባችን ምኞታችን ነው::ያላወቁን የወደፊት ልጆቻችንን ለማስተማርና ለማስጠንቀቅ አስበን በጀርመን ህጋዊ አካልነት ያገኘው ማህበራችን አነሳሽነት የጀመርነውን ድህረ ገጽ አንባቢ እንዲያገኝና ብዙ ወጣቶች እንዲጠነቀቁ Link በማድረግ እንድትረዱን እንጠይቃለን

በዛሬው እለት እኛ ከዚህ በታች ስማችንና አድራሻችን የተዘረዘረው የአገራችሁ ወንድሞች ወደ እናንተ የተከበራችሁና በተለያየው መንገድ የአገራችሁን ህዝብ በተለያየ የመገናኛው ብዙሀን ማእከል ሆናችሁ ህዝባችሁንና እኛን ስለምታገለግሉ አክሮታችን ክልክ በላይ ነው::

ይህንንም ታልቅ ስራ ስለምታከናውኑና እስካሁንም ህዝባችንን በተለያየ መንገድ ስለረዳችሁ አሁንም ይህንን ታላቅ አገር ወዳድነታችሁን በተደጋጋሚ በብዙ ዜጎች ላይ ካየነው ጥቃት የተነሳ ዜጎችን በአለም አቀፍ ደረጃ ከተደራጁ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ከጥፋትና ከመጥፎ መንገድ እንዲሁም ከብዙ አስከፊ መንገዶች ሳያውቁ ገብተው እንዳይጠቁ ለማስተማር በጀርመን ህጋዊ አካልነት ያገኘው ማህበራችንን ለማስተዋወቅ በተለያዩ መገናኛ ብዙሀን ህዝባችንን የማስተማር ሂደቱን እስክናስፋፋ ድረስ በመጀመሪያ ደረጃ ከውጪ አገር ዜጎች ጋር በመተባበር ወደ ህይወት የጠራነውን ድህራ ገጻችንን http://www.saveethiopians.net/index.html እንዲታወቅ ወይም ሌሎች እንዲያዩት Link በማድረግ እንድትረዱን የመተባበር ጥያቄ እናቀርባለን::

ይህ ጉዳይ በአገራችን እንዲሁም በውጪ አገር የብዙ ወጣቶች ሴቶችንንና ሕጻናትን ህይወት በቀጥታ የሚዳስስ በመሆኑ እንደሌላው አገር ይህንን አይነት ድርጊቶችን በአገራችን የሚከላከል መንግስታዊ አካል ባለመኖሩ በአብዛኛው በስህተት ህይማኖታዊ ትምህርትና ወንጀልን የሚሰሩ ድርጅቶች ተጠቂ የሚሆኑ ዜጎች የሚተርፋቸው እብደት: በሽታ: በየጸበሉ መንከራተትና ለተለያየ ፍርሀት ጭንቀትና የስነልቦና ችግር እነርሱና ቤተሰቦቻቸው በቻቸውን ተጋልጠው መቅረት ነው::

ይህንን ችግር የተረዱ የምእራብአዊያን አገሮች በሚንስቴር ደረጃ በሚንቀሳቀሱ ክፍሎች ስር http://www.saveethiopians.net/Links.html በተለያየ መንገድ ህዝባቸውን የሚያስተምሩና የሚያስጠነቅቁ ሲሆን ይህንን የመጀመሪያውን የግል አነሳሽነት እኛ ብናደርገው መንግስትም በሚችለው ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ህዝብን ያስተምራል ብለን ስለምናመን ይህንን እውነት ወደህዝባችን ለማድረስ በምናደርገው ብዙዎችን የወደፊት ወጣቶች ለማዳን ተጋድሎ እናንተም በየድህረ ገጻችሁ ላይ እንድትተባበሩን በማህበራችን ስም እንጠይቃለን

Ethio-Cult Information Centre e.v.
የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው:
ክቡር አቶ ፍሰሀ ደስታ (ሊቀመንበር:- 0491623350595)
ኢንጂነር አበበ ሀይሉ (ጸሀፊ :- 04917624355016)
አቶ ቶማስ አሰፋ(MSC . የኮሜርስ ኮሌጅ ላይብረሪ አላፊ የነበሩት የውጪ ግንኙነት 07022977489)
አቶ መሳፍን ል/ሰገድ(በጀርመን የኢትዮጵያ ሬስቶራንት ባለቤት:- ሂሳብ ክፍል 0497115920137)
Hr. Schmid Wolfgang(MSC የህግ አማካሪ 0711558368)